Alexandria City Public Schools EQUITY FOR ALL

T.C. TITAN NEWS

News from T.C. Williams High School

King Street • Minnie Howard • International Academy • Satellite

## አገስት 24፣ 2020

**የተከበራችሁ  የቲታን ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና  ጎደኞች**

ይህ የዜና መፅሄት በ2020-2021 የትምህርት ዓመት በሴፕቴምበር 8 ቀን ወደ ትምህርት ቤት ስንመለስ ስለሚኖረው የቲታን ቨርችዋል ፕለስ የጊዜ ሰሌዳ ማብራሪያ እንደሚሰጥ ተስፋ አደርጋለሁ።  የእኛ ሰራተኞች ተገቢውን  ምክር ለመስጠት፣ ለጥያቄዎ መልስ እንደሚሰጡ እና ሌላ የሚፍልጉትን ድጋፍ   ተዘጋጅተው የሚጠብቁ መሆኑን እንደሚረዱ ተስፋ አደርጋለሁ።

የቲታን ቨርችዋል ፕለስ የኤ.ሲ.ፔ.ኤስ. የዘርፈ-ብዙ ስራ እቅድ አዘጋጅ ቡድኖች ት/ቤቶች መልሶ ለመክፈት  እቅድ አካል በመሆን የጊዜ ሰሌዳ የተዘጋጀው ነው። ሁሉንም ሊፈጠሩ የሚችሉ ነገሮች ያገናዘበ የድብልቅ የጊዜ ሰሌዳ ጨምሮ ፣ ሙሉ በሙሉ ቨርችዋል የጊዜ ሰሌዳ  እና  በአካል  በመገኘት የሚሰጥ ትምህርት የተዘጋጀ ያካተተ ነው።  የጊዜ ሰሌዳው የተወሰነው ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በቨርችዋል በሴፕቴምበር እንደሚሰጥ  ባሳወቀበት ወቅት የተገለፀ ሲሆን ጠቃሚ የሆኑ ጥቂት ነገሮች አብሮ ያከተተ መሆኑን ተገልፃል። የተማሪው እና የአስተማሪው ቨርችዋል የስራ መጠን፣ እና ከእኛ የስፐሪንግ ወቅት ቨርችዋል ልምድ የተወሰዱ ለተማሪው ጠቃሚ የሆነ ልምዶች።  ይህ የጊዜ ሰሌዳ  ለተማሪዎች ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ፍትሃዊ የሆነ እድሎችን እንደሚፈጥር አምንበታለሁ።

የቲታን የቨርችዋል ፕለስ የጊዜ ሰሌዳ  በቨርችዋል ክፍል ውስጥ  ለማስተማር እና  ለተማሪዎች ለመማር አዲስ እውቀት ለማስተማር፣ የማስተማር ድጋፍ ለማድረግ ፣ ከአስተማሪዎችና ሰራተኞች ጋር ግንኙነቱን ለመፍጠር  እና ተማሪዎችን የትምህርት ቤት ኮሚዮኒቲ ግንኙነታችውን እንዲጠብቁ ለማደረግ ያግዛል።   በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ የቨርችዋል ፕለስ+ የጊዜ ሰሌዳ የሚያካትተው የሲንክሮኒክስ እና አሲንክሮኒክየስ ትምህርት ጊዜ የያዘ ሲሆን የሴምስተር ቆይታ ወይም የአንድ ሙሉ የትምህርት ዓመት የሚቆይ ሊሆን ይቻላል።  ከታች ያለው መረጃ የጊዜ ሰሌዳውን የበለጠ ለመረዳት እንደሚያግዝ ተስፋ አደርጋለሁ።

### የቲታን የቨርችዋል ፕለስ የጊዜ ሰሌዳ

<u>ሰኞ የሳምንቱ የመጀመሪያ  ቀን</u>

በየሳምንቱ ሰኞ ለሰራተኞች የእቅድ ማውጫ ጊዜ ነው እና ለተማሪዎች ደግሞ የአሲንክሮኒክስ የትምህርት ቀን ነው።

- የእኛ ሰራተኞች በመላ ትምህርት ቤቱን ያቀፈ ስብሰባ በማካሄድ ያሳልፉሉ፣ የሙያ ስልጠና ትምህርት፣ በትምህርት ይዘት ላይ የተመሰረተው የሙያ ትምህርት ኮሚዩኒቲ(PLC) ስበሰባዎች እና ለሳምንቱ ትምህርት የግል የትምህርት ዝግጅት  ያደርጋሉ።

- ተማሪዎች የአሲንክሮኒክስ የትምህርት ሲሰሩ ይቆያሉ።   በአሲንክሮኒክስ የትምህርት ቀናት ተማሪዎች ተለዋዋጭ  እና ፍትሃዊ የሆነ እድል ያገኛሉ ቀኑን ሙሉ ለማከናወን እድል ያገኛሉ።  የአሲንክሮኒክስ የትምህርት እንቅስቃሴዎች በካንቫስ ውስጥ ያገኛሉ። የተለያዮ እንቅስቃሴዎች ያካትታሉ እና የመማሪያ ድጋፍ ሪሶዋርሶችን ያገኛሉ ለምሳሌ፤ የተቀዱ የማስተማሪያ ቪዲዮዎች እና የኦንላይን የቤት ስራዎች።  ይህ ጊዜ ትምህርት ለመከለስ እና ክሬዲት ለማሻሻል ሊውል ይችላል።

<u>ከማክሰኞ  እስከ  አርብ  በቀጥታ የሚተላለፍ  የትምህርት  አሰጣጥ</u>

ከማክሰኞ እስከ አርብ በቀጥታ የሚተላለፍ የሲንክሮኒክየስ ትምህርት ቀናት  ቀኑ የሚጀምረው ጥዎት 8.30 ሲሆን የሚያቆመው ከቀኑ 3.15 ላይ ነው።

- በቀጥታ  በአስተማሪ የሚሰጥ ትምህርት ክፍል የሚወስደው ጊዜ ከ50 እስከ 60 ደቂቃ  ይሆናል ።

- እንዲሁም  የአሲንክሮኒክየስ  ትምህርት ጊዜ በቲታን የቨርችዋል ፐለስ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ በ8.30 ጦት የሚጀመረው በታሳቢነት ተካቶል።

- በየሰዓቱ ተማሪውን ስለመገኘቱ የስም ጥሪ ይኖራል

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች  የትምህርት ቀን የሚጀምረው በአሲንክሮኒከየስ  ትምህርት የጊዜ ሲሆን ከጥዎት 8.30 እስከ 10.00 ድረስ ይሆናል።

- ይህ ጊዜ የተመደበው  ለአሲንክሮኒከየስ ትምህርት የጊዜ ሲሆን ተማሪዎች በካንቫስ የተሰጠው የቤት ስራ የሚሰሩትበት ጊዜ ይሆናል።
- በተጨማሪ በዚህ በተመደበው የጊዜ ሰሌዳ ወቅት የሲንክሮኒክስ የተመረጡ ድጋፎች ለተማሪዎች የሚሰጥበት ወቅት ነው።  ለምሳሌ አስተማሪዎች የተወሰኑ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ቡድኖች በተወሰኑ ርእሶች በሚመልከት የተለየ ድጋፍ እና የቤት ስራዎችን በሚመለከት ምክክር ለማድረግ ሊውል ይችላል።

<u>የመጀመሪያ ምድብ ጊዜ (ብሎክ) አንድ ዓመቱ የሚቆይ ክፍለ ጊዜ</u>

በ10.00 ጥዎት ተማሪዎች ወደ መጀመሪያ ምድብ ጊዜ ክፍለ ጊዜ ይገባሉ። ይህም ብሎክ  1 ተብሎ ይጠራል።

- የመጀመሪያው ክፍል ጊዜ የሚደረገው ግንኙነት 60 ደቂቃዎች ይቆያል  ይህ ሁሉም የቲታን የሚገባበት ይሆናል ዓመቱን በሙሉ የሚቆይ የትምህርት ዓይነት የሚከታተሉበት እንዲሁም የማህበራዊ፣ የስሜት  የአካዳሚ ትምህርቶች (SEAL) የሚከታተሉበት ነው።  በተለይ በዚህ ጊዜ  ተማሪዎችን ለማገዝ በጣም አስፈላጊ ይሆናል።
- በድጋሚ ይህ ክፍል ዓመቱን ሙሉ የሚካሄድ ነው።

<u>ምሳ እና የአእምሮ ማሳረፊያ</u>

ተማሪዎች እና ሰራተኞች ከዚህ ግዜ በኋላ  ከ11.00 ጥዎት እስከ እኩለ ቀን ድረስ የምሳ የእረፍት ጊዜ ይኖራቸዋል።

<u>ብሎክ  3 ፣  5 እና 7 ሲንክሮኒከየስ ትምህርት ጊዜ</u>

ከማክሰኞ እስከ አርብ በቀጥታ የሚተላለፍ ከእኩለ ቀን ጀምሮ ተማሪዎች ሶስት ተጨማሪ የሲንክሮኒከየስ ትምህርት ብሎክ ክፊለ ጊዜ ይኖራቸዋል።

- በአንደኛ ሴምሲተር በእነዚህ የክፍለ-ጊዜያት ብሎክ 3 ፣  5 እና 7 ተብለው የተሰየሙት እያንዳንዳቸው ለ50 ደቂቃ ይቆያሉ በመሃል 20 ደቂቃ እረፍት ይኖራል።
- በእነዚህ የክፍል ጊዚያት ተማሪዎች በሴምሲተር የሚቆዩ ትምህርቶች ይከታተላሉ እና በቀጣት በአስተማሪ የሚሰጥ ከፍተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ እና ማብራሪያዎች የሚሰጡበት ትምህርት ይከታተላሉ። ይህም ማለት ተማሪዎች ዝም ብለው የኮምፒወተር መስኮቱን የሚመለከቱበት ጊዜ ይሆናል ማለት አይደለም።  የእኛ ሰራተኞች ከቴክኒዋሎጂ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ እና ራሳቸው በንቃት ተሳታፊ ለማድረግ ይሰራሉ።

በሴምሲተሩ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች በተሟላ መልኩ የብሎክ 3፣ 5 እና 7 ኮርሶችን ያጠናቅቃሉ።  ተማሪዎች ዓመት በሚወስዱ ኮርሶች የሚሳተፉ በእነዚያ ኮርሶች ላይ ይቆያሉ በሁለተኛ ሴምሲተር ወቅት።

<u>ሁለተኛ ሴሚስተር ብሎክ  2 ፣ 4 እና 6</u>

በሁለተኛ ሴሚስተር ወቅት ተማሪዎች  የሲንክሮኒክስ ትምህርት ከጥዎት 8.30 እስከ 10.00 ድረስ ይቀጥላሉ እና የብሎክ አንድ የዓመቱ ቀጣይ የሲንክሮኒክስ ትምህርት ከ60 ደቂቃ ከ10.00 ጥዎት እስከ 11.00 ድረስ ይከታተላሉ።   ከሴሚስተር አንድ የተለየ ነገር የለም።

- ተማሪዎች አሁን ሶስት አዲስ የሲንክሮኒክስ ክፍል ይኖራቸዋል ብሎክ 2፣ 4 እና 6 የሚባሉ ኮርሶች።  በሁለተኛው ሴምሲተሩ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች በተሟላ መልኩ የብሎክ 1፣ 2 ፣ 4 እና 6 ኮርሶችን ያጠናቅቃሉ።

ስለሆነም በትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች 7 ኮርሶችን ማጠናቀቅ ይችላሉ በተለመደው የትምህርት ዓመት ላይ የሚያጠናቅቁትን።

<u>የሴምሲተር ቆይታ ያለው ወይም የዓመት ቆይታ ኮርስዎች</u>

የእኛ ቲታንፐለስ የጊዜ ሰሌዳ ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች በይዘቱ ላይ እንዲያተኩሩ ያስችላቸዋል የክሬዲት የማሻሻያ ግዜ ከመስጠት ባሻገር።  የሴሚስተር ቆይታ ያላቸው ኮርሶች ሞዴል ለተማሪዎች ትንሽ ስራ ማለት አይደለም። ሆኖም ግን በአንድ ጊዜ ጥቂት ክፍሎችን ማስተናገድ ማለት መሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው ።

- በሁለተኛ ሴምሲተር ወቅት ተማሪዎች ከ8.30 ጥዎት እስከ 10.00 ድረስ ያለውን ክፍለጊዜ  ለአዳንቫስ ፐሌስሜንት (AP)፣ ለጥምር ፕሮግራም (DE) ለመከታተል እና ለትምህርት ይዘት ለማጥናት መጠቀም ይችላሉ።

ሆኖም ግን ጥቂት ኮርሶች ዓመቱን በሙሉ መቀጠል ይኖርባቸዋል። ይህ ጊዜ የሚፈልጉ የኮርስ ዓይነቶች፤ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ኮርሶች፣ የተወሰኑ የአዳንቫስ ፕሌስሜንት ኮርሶች (AP) እና ለተማሪዎች የEL እንዲያገኙ የተዘጋጁ የተወሰኑ ኮርሶች ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ያካትታል። ሌሎች ኮርሶች ለምሳሌ የትርዒት አርት በተጨማሪ ዓመቱን ሙሉ እንዲሰጡ ይደረጋል።

አንዳንድ የAP ኮርሶች ዓመቱን በሙሉ የሚካሄዱ ሊሆን ይችላል ሌሎች ደግሞ በሴሚሲተር ብቻ የሚወሰኑ ይሆናሉ። እነዚህን ውሳኔዎች ስንወስድ ትልቅ ጥንቃቄ አድረገናል። የኤ.ፒ. (AP) ፈተናዎች የሚካሄዱት በሜይ ወር እንደሆነ እንረዳለን። ስለሆነም ተማሪዎችን ድጋፍ ለመስጠት ለአንደኛ ሴሚስተር ብቻ ለማደረግ ፌብሩዋሪ ፣ ማርች እና ኤፕሪል ተማሪዎች ለኤ.ፒ.(AP) ዝግጁ መሆናቸው ለማረጋገጥ ከጥዎት 8.30 እስከ 10.00 ሰዓት ድረስ ያላውን ጊዜ የጊዜ ሰሌዳ እንጠቀማለን። የኮሌጅ ቦርድ ጠቃሚ የሆነ የመማሪያ ማቴሪያል አዘጋጅቶል ለአስተማሪዎችና ለተማሪዎች የሚጠቀሙበት በእነዚህ ጊዜያት ከፈተና አስቀድሞ አዳዲስ ነገሮች እንዲጨብጡ ለማድረግ ።

የተማሪው የጊዜ ሰሌዳ (ስኬጅውል) በሚወስዱት ኮርሶች የሚወሰን ነው እና የኮርስ ምርጫቸውን ከዋናው የጊዜ ሰሌዳ ጋር በማስተያየት ሁልግዜም በየዓመቱ እንደሚደረገው ሁሉ። አንድ ተማሪ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ከአንድ ኮርስ በላይ ከመረጠ ተማሪው ከአንድ በላይ ኮርስ ሊወስድ ይችላል። ይህም ባላቸው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ እንዲስማማ ይደረጋል። በሴፕቴምበር መጀመሪያ ላይ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የተወሰኑ መረጃዎችን የያዙ የጊዜ ሰሌዳቸው ይደርሳቸዋል የሚወስዶቸው ኮርሶች የትኛው ዓመቱን እንዲቀጥል የትኛው በሴሚስተር እንደሚጠናቀቅ የሚገልፅ ።

አንዳንዶች ነገሮች አዲስ ሊመስሉ እንደሚችሉ እረዳለሁ እና አንዳንዶች ደግሞ የተለመዱ የሚታወቁ ናቸው። እባክዎን ይገንዘቡ እኛ እዚህ ያለውን ለእናተ እገዛ ለማድረግ ነው! የእኛ የትምህርት ቤት አማካሪዎች፣ አስተማሪዎች እና ሁሉም የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በቅርብ ጊዜ ወደ ስራ ይመለሳሉ። ስለሆነም እገዛ ወይም እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ ከእኛ ጋር ይገናኙ። የ2020-2021 የትምህርት ዓመት በተጠናከረ ሁኔታ ለመጀመር በጉጉት እንጠብቃለን።

ከምስጋና ጋር፣

ፒተር ባላሥ (Peter Balas) ርእሰ መምህር
የቲ.ሲ. ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
የኪንግ ስትሪት ግቢ
ሚኒ ሐዋርድ ግቢ
ሳታላይት ግቢ (ካምፓስ)

በቲወተር ገፅ ያግኙኝ ፤ @TCWprincipal